# <u>የልጅነት፡ ክብር - የእግዚአብሔር፡ ወራሽነት</u>

የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ “ልጆችም፡ ስለ፡ ሆናችሁ፡ እግዚአብሔር፡ አባ፡ አባት፡ ብሎ፡ የሚጮኽ፡ የልጁን፡ መንፈስ፡ በልባችሁ፡ ውስጥ፡ ላከ። ስለዚህ፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ ልጅ፡ ነህ፡ እንጂ፡ ባሪያ፡ አይደለህም፤ ልጅም፡ ከሆንህ፡ ደግሞ፡ በክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር፡ ወራሽ፡ ነህ፡ (ገላቲያ 4፡6-7) ይለናል። ባለፈው፡ ሳምንት፡ ከልጅነታችን፡ የተነሳ፡ የተሰጠንን፡ የልጅነት፡ መንፈስ፡ ተመልክተናል። ዛሬ፡ ደግም፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ በመሆናችን፡ በክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር፡ ወራሾች፡ የመሆናችንን፡ ሚስጢር፡ እናያለን። በምድራዊ፡ ህግ፡ ወራሽ፡ በሞት፡ የማይቋረጡን፡ የአውራሹን፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች፡ በመውሰድ፡ የአውራሹን፡ ትሩፋት፡ ያስቀጥላል። አውራሹ፡ እጅግ፡ ባለጠጋ፡ የነበረ፡ ከሆነ፡ ይህ፡ ባለጠግነት፡ ወደ፡ ወራሹ፡ ይመጣል። ከዚህም፡ የተነሳ፡ በምድር፡ በዙ፡ ሃብት፡ ያለው፡ ሰው፡ ወራሽ፡ መሆን፡ ትልቅ፡ እድል፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ እንደሚያረጋግጥልን፡ እኛ፡ በክርስቶስ፡ አምነን፡ የዳንን፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ በክርስቶስ፡ ሆነን፡ የእግዚአብሔር፡ ወራሾች፡ ሆነናል (ሮሜ 8፡17)። ይህ፡ በጣም፡ አስደናቂ፡ የሆነ፡ ከመታሰብ፡ የሚያልፍ፡ ክብር፡ ነው። እንዴት፡ ሰው፡ የሰማይና፡ የምድር፡ ፈጣሪና፡ ባለቤት፡ የሆነው፡ ዘላለማዊ፡ አምላክ፡ ወራሽ፡ ይሆናል? ይህንን፡ የርስት፡ ባለጠግነት፡ ለመረዳት፡ ሐዋሪያው፡ ጳውሎስ፡ ለኤፌሶን፡ አማኞች፡ እንደጸለየው፡ የውስጥ፡ መገለጥ (የልቦናችን፡ አይኖች፡ መብራት) ያስፈልገናል።

እግዚአብሔር፡ በክርስቶስ፡ የእርሱ፡ የራሱ፡ ወራሾች፡ ሲያደርገን፡ የአንድ፡ ልጁን፡ ክብርና፡ ስፍራ፡ ሰጥቶናል። ከዚህም፡ የተነሳ፡ (1) ከክርስቶስ፡ ጋር፡ በሰማያዊ፡ ስፍራ፡ አስቀምጦናል። የክብርና፡ የምስጋና፡ አክሊልም፡ ተሰጥቶን፡ የክርስቶስ፡ ወንድሞች፡ ተብለን፡ ተጠርተናል። ክርስቶስም፡ ወንድሞቼ፡ ብሎ፡ ሊጠራን፡ አያፍርም። (2) የእግዚአብሔር፡ የራሱ፡ ወራሾች፡ በመሆናችንም፡ እግዚአብሔርን፡ ለመምሰል፡ የሚሆነው፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ተሰጥቶን፡ የመለኮት፡ ባሕርይ፡ ተካፋዮች፡ ሆነናል (2 ጴጥ 1፡2-4)። በባህርይ፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፣ ምህረትና፡ ሰላም፡ ተካፋዮች፡ ሆነናል። ይህም፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር፡ ኃይል፣ ታምኝነትና፡ እውነተኝነት፡ ከኛ፡ ጋር፡ ሆኗል። (3) ልክ፡ እግዚአብሔር፡ ለሌዊ፡ እድል፡ ፈንታው፡ እንደነበረ፡ እንዲሁ፡ እግዚአብሔር፡ እድል፡ ፋንታችን፡ ሆኗል። የእግዚአብሔር፡ የሆነው፡ ሁሉ፡ ለኛ፡ ሆኗል።

ወገኖቼ፡ በተከታታይ፡ እንዳየነው፡ እግዚአብሔር፡ በበደላችንና፡ በኃጢያትችን፡ ሙታን፡ የነበርነውን፡ ሰዎች፡ አለ፡ ልክ፡ ነው፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደረገን። በተሰጠን፡ የልጅነት፡ ስልጣን፡ የተቀዳጀነው፡ ክብር፡ እጅግ፡ የላቀ፡ ነው። ይህ፡ ሁሉ፡ የሆነልን፡ ከእግዚአብሔር፡ ፍቅርና፡ ምህረት፡ የተነሳ፡ ነው። ክርስቶስ፡ በጌተሰማኒ፡ የደም፡ ላብ፡ ያላበው፣ “ኤሎሄ፡ ኤሎሄ፡ ላማ፡ ሰበቅታኒ” ብሎ፡ የቃተተው፣ አምላክ፡ አንድ፡ ልጁ፡ የሰው፡ ልጆችን፡ ሃጢያት፡ ሁሉ፡ እንዲሸከም፡ የፈቀደው እኛ፡ ወደዚህ፡ ክብር፡ እንድንደርስ፡ ነው። ክርስቶስ፡ የተናቀ፣ የተጠላ፡ የህማም፡ ሰው፡ ሆኖ፡ እኛን፡ ወደ፡ ክብር፡ አመጣን። አምላክነትን፡ እንደ፡ መቀማት፡ ሳይቆጥር፡ እራሱን፡ ባዶ፡ አደርጎ፡ ሰው፡ በመሆን፡ ከሞት፡ ፍረሃንት፡ ነጻ፡ አድርጎ፡ መንድሞቼ፡ ብሎ፡ ጠራን። ወገኖቼ፡ የሄ፡ እንዴት፡ ያለ፡ ፍቅር፡ ነው? ይህ፡ ምህረት፡ ከምን፡ ጋር፡ ሊወዳደር፡ ይችላል? ቅዱሳን፡ እናስተውል፡ በክርቶስ፡ ያገኘነው፡ ስፍራ፡ ገና፡ ለዘላለም፡ የሚያስደንቀን፡ ነው። እኛን፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ የልጅነታችንን፡ ክብር፡ መገለጥ፡ የሚጠባበቀውን፡ አሁን፡ በጥፋት፡ ባርነት፡ የተያዘውን፡ ፍጥረት፡ ሁሉ፡ ገና፡ የስደንቃል።